# የይሖዋ ምስክሮች ኑፋቄ

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የዓለም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

## መግቢያ

*በስመ አብ ወወልድ                    አምላክ አሜን፡፡*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የአምላክ መጠሪያ ስም ሆኖ ያገለግል የነበረውን «ያህዌ» የሚለውን ስም በመውሰድ ራሳቸውን «የይሖዋ ምስክሮች» ነን በማለት የሚጠሩት የእምነት ተከታዩች ክርስቲያን የሚለውን ስም መጠቀም ካለመፈለጋቸውም የተነሣ በዚህ ስም በፍጹም አይጠሩም፡፡ ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ እቀበላለን ቢሉም በፍጹም ክርስቲያኖች አይደሉም፡፡ እንዲያውም አዲስ ኪዳንን ለራሳቸው እንደሚመች አድርገው አሳሳች በሆነ መንገድ ተረጉመውታል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ያላቸው አስተምህሮ ከአማናዊቷ ቤተክርስቲያን ትምህርት ሙሉ በሙሉ የተለየ ከመሆኑም በላይ ከአርዩስና ሌሎች የዘመናችን አዳዲስ የኑፋቄ ትምህርቶች ጋር የተቀላቀለ ነው በአሁኑ ጊዜ የዚህ እምነት ተከታዩችና ክህደታቸው ከተወገዘው ከአርዩስ በበለጠና በላቀ ሁኔታ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

የይሖዋ ምስክሮች ቤተክርስቲያንና በዓለም መንግሥታት ሁሉ የሰይጣን ሥራ ውጤቶች ናቸው በማለት ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም ዜጎች በወታደራዊ ተቋማት ውስጥ እንዳይገቡ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ግፊት ያደርጋሉ፡፡ ለሰንደቅ ዓላማ የክብር ሰላምታ መስጠትን እንደ ባዕድ አምልኮ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

በመሆኑም በዓለማችን የሚገኙ የብዙ አገሮች መንግሥታትም በአገራቸው አጠቃላይ ሰላም ላይ የይሖዋ ምስክሮች የሚያስከትሉትን ከባድ አደጋ በመገንዘብ ከሀገር እንዲባረሩ አድርገዋቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሣት «የይሖዋ ምስክሮች» ኑፋቄን ብቻ ሳይሆን አደገኛ የፖለቲካ አስተሳሰቦችን ጭምር እንደሚነዙ መናገር ይቻላል፡፡

የይሖዋ ምስክሮች የሰው ልጅ ነፍስ አትሞትም የሚለውን እምነት አይቀበሉም እንዲያውም ይህ እምነት የሰይጣን አስተምህሮ ነው ብለው በፅኑ ያምናሉ፡፡ የሰው ልጅ ከትንሣኤ በኃላ ገነት በምትሆነው ምድር ለዘላለም ይኖራል በሚል እምነት በመታሰራቸው እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጅ የገባውን የሰማያዊ መንግሥት ቃል ኪዳን ይቃረናሉ፡፡

## የይሖዋ ምስክሮች ኑፋቄ

### *ታሪካዊ ገጽታ*

የይሖዋ ምስክሮች የተባለው ተቋም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በሃይማኖት ስም የተመሠረተ ድርጅት ሲሆን መሥራቹም እ.ኤአ በ1854 በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፔንሳልቫንያ (Pennsylvania) በምትባለወ ግዛት ውስጥ የተወለደወ ቻርልስ ራስል ነው፡፡

ራስል ቀደም ባሉት ጊዜያት ክርስቲያን የነበረ ሲሆን በኃለኛው የወጣትነት ዘመኑ በአርዩሳውያን የኑፋቄ ትምህርትና በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት እንዲሁም በአንዳንድ የክህደት እግዚአብሔር ትምህርት (Atheists) አራማጆች ተፅዕኖ ሥር ወደቀ፡፡ እ.ኤ.አ በ1872 አካባቢ ከነዚህ የተበረዙና የተዛቡ አስተምህሮዎች በመነሣት ራስል የራሱን አስተምህሮ (Doctrine) በመቅረፅ በዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ ውስጥ ለማሳተም ቻለ፡፡ ቻርልስ ራስል በሀብት በኩል ሲታይ ለኢንድስትሪ ማስፋፊያና ለንግድ ፕሮጀክቶች ይጠቀምበት የነበረ ግምቱ ወደ አምስት ሚሊዩን ዶላር የሚጠጋ ሀብት ለማከማቸትም በቅቶ ነበር፡፡

የቻርልስ ራስል የግል ሕይወትን ስንመለከት በጋብቻ እምነት በማጉደል ምክንያት በሚስቱ ተከሶ ጉዳዩ በሐሚልተን ፍርድ ቤት ከታየ በኃላ የገንዘብ ቅጣት የተበየነበት ሲሆን ሚስቱም ላቀረበችው የፍቺ አቤቱታ የፍቺ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣት ወስኖላታል፡፡ በተጨማሪም የሀገሪቱ ገበሬዎች በፈፀመባቸው የማጭበርበር ወንጀል ክስ መሥርተውበት ነበር፡፡ ገበሬዎቹ ራስልን እንዲከሱት ያስገደዳቸው ዐቢይ ምክንያት ራስል ተራና የተለመደውን የአሜሪካ

ስንዴ «ተአምራዊ ስንዴ» የሚል ቅጽል ስም በመስጠትና ከቅድስቲቱ ምድር የተገኘ ነው በማለት ስንዴው የተትረፈረፈ በረከት እንዳለው በመስበክ አጭበርብሮ በውድ ዋጋ በመሸጡ ነበር:: በኃላ ላይ ስንደው እንደተባለወ ሳይሆን ተራና የተለመደ ሆኖ በመገኘቱ ገበሬዎቹ በሕግ ፊት ሊያቀርቡት ችለዋል::

እ.ኤ.አ በ1878 ላይ ራስል በዓለማችን ላይ የሚገኙትን ሁሉንም የክርስትና እምነት ትምህርቶች በይፋ ተቃወመ:: እ.ኤ.አ በ1879 «የመጠበቂያ ግንብ (Watch Tower) » የተባለውን መጽሔት አሳተመ:: እ.ኤ.አ በ1884 ያላቸውን የበራሪ ጽሑፎች ማኅበርን አንድ ላይ በማቀናጀት ለማዋሐድ ቻለ::

ቻርልስ ራስል እ.ኤ.አ በ1916 ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ጀጅ ዩሴፍ ራዘርፎርድ(Judge Joseph Rutherford) ቦታውን ተክቷል::

## ሐሰተኛ ትንቢቶቻቸው

በይሖዋ ምስክሮች ከተነገሩት እጅግ አስገራሚ ትንቢቶች መካከል አንዱ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትን በተመለከተ ነው:: ራስል «እ.ኤ.አ 1914 ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር የዓለም ፍጻሜ ይሆናል:: አይሁድ ሁሉ አንድ ላይ ተሰብስበው ዓለምን ያስተዳድራሉ» ተናግሯል:: ነገር ግን ትንቢቱም ሳይፈጸም ቀርቷል:: እርሱም እ.ኤ.አ በ1916 ሞቷል::

ከዚህ በኃላ የይሖዋ ምስክሮች አስተሳበባቸውን እደሚከተለው ለመቀየር ተገደው ነበር:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግጥ እ.ኤ.አ በ1874 በአካል ባይመጣም በመንፈስ መጥቷል:: እናም እ.ኤ.አ በ1878 «የተመረጡትን» መሰብሰብ ጀመረ:: እ.ኤ.አ በ1914 ደግሞ አብ /ይሖዋ/ የንግሥና ዘውድ ጭኖለት የሾመው በኃላ መፍረድ ጀመረ የሚል ትንቢት የተተነበየ ሲሆን በዚህ ትንቢት ምክንያት ብዙ ሰዎች ለዓለም ፍጻሜና ለመጨረሻው ፍርድ ዝግጅት ሲሉ ንዛዜያቸውን በወረቀት በማስፈር ሀብቶቻቸውን ሁሉ ለይሖዋ ምስክሮች ሰጥተዋል::

የራስልን ቦታ የተካው ራዘርፎርድም በበኩሉ በተናገረው ትንቢት የነቢያት ሁሉ አባት የሆነው አብርሃም ከነቢያት ጋር በቡድን በመሆን እ.ኤ.አ በ1925 ወደ ምድር እንደሚመጣ ተናገረ:: ከዚያም አብርሃምንና ነቢያቱን ለመቀበል በካሊፎርኒያ ውስጥ 75.000 ዶላር የሚያወጣ ቤተ መንግሥት አዘጋጀ:: ራዘርፎርድ እንግዶች ያላቸውንና እስካሁን ድረስ ያልመጡትን ነቢያት ባዘጋጀው ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚስቱ ጋር ሲጠብቅ ኖሯል::

## የይሖዋ ምስክሮች ክርስቲያኖች አይደሉም

የይሖዋ ምስክሮች በአዲስ ኪዳን እናምናለን ቢሉም ክርስቲያን የማለውን ስም በፍጹም የማይቀበሉና ከክርስቶስ ጋር ምንም ዓይነት ኀብረት የሌላቸው ሲሆኑ ግንኙነታቸው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት የአምላክ ስሞች አንድ ከሆነው «ያህዌ» ከሚለው ስም ጋር ብቻ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች በክርስቶስ ፍጹም የማያምኑ ከመሆናቸውም ባሻገር ምንም ልዩነት ሳያደርጉ ማንኛውንም ሃይማኖትን እንደሚነቅፋና እንደሚያጠቁ ሁሉ የክርስትና ሃይማኖትንም በፅኑ ይቃወማሉ::

ለራሳቸወ እንደሚመችና እንዲስማማ በማድረግ ከውስጡ ብዙ ነገሮችን የሰረዙበትና የለወጡበት የአዲስ ኪዳን ትርጉሞችን በፍጹም አይቀበሉም:: ይህም በመሆኑ ጥቅስ እየጠቀሱ ከእነርሱ ጋር ሰፊ ውይይት ማድረግ ፍሬቢስ ነው::

## የይሖዋ ምስክሮች ቡድን አደገኛ ድርጅት ነው

የይሖዋ ምስክሮች የዓለም መንግሥታትን ሁሉ የሰይጣን ሥራ ውጤት አድርገው ይመለከታሉ:: ወታደራዊ ተቋማትን አይደግፋም:: እነዚህን ተቋማት እንደ ሰይጣን ሥራ ውጤቶች አድርገው ያስባሉ:: ማናቸውንም ወታደራዊ ተግባራት ይቃወማሉ::

## የይሖዋ ምስክሮችና የኅትመት ውጤቶቻቸው

የይሖዋ ምስክሮች የሚያሰራጯቸው አያለ መጻሕፍት ፓምፕሌቶችና በራሪ ጽሑፎች አሏቸው:: በጣም ታዋቂ ከሆኑት መጻሕፍት መካከል እውነት ነው የአምላክ በገና በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ ዕውቀት መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ ቃል ወይስ የሰው? የሚሉና ሌሎችም ይገኙባቸዋል::

### *እምነታቸው*

የይሖዋ ምስክሮች የጥንቱና የዘመናችን መናፍቃን ስብስብ ናቸው ማለት ይቻላል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉማቸው የአዲሲቱ ዓለም መጽሐፍ ቅዱስ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ትርጉማቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ሥርዓት ነጥብ በመቀየር ቃላትን በማውጣትና በማስገባት ለራሳቸው እንደሚመችና እንደሚስማማ አድርገው ለውጠውታል::

_ስምሳሌ:-_ የሰው ልጅ ነፍስ ዘላለማዊ እና የማትሞት መሆኗን አያምኑም:: ልክ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት እምነት ተከታዮች ሁሉ ነፍስ ሕያው አይደለችም ብለው ያምናሉ:: የሰው ልጅ ሲሞት ምንም አያውቅም አይሰማውም ሕይወትም አይኖረውም እንዲሁም ራሱንም መገንዘብ አይችልም ብለው ያምናሉ:: ይህ እምነታቸው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ቁጥር 43 ላይ ጌታችን በቀኙ ለተሰቀለው ወንበዴ «እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ::» በማለት የገባለትን ቃል ኪዳን ይቃረናል:: ይህ ከፋ አድራጊ በገነት ከክርስቶስ ጋር እስከሆነ ድረስ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እስከሆነ ድረስ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የኅብረቱ ተሳታፊ የሚያደርገው ሕያው ነፍስ አለው::

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የዚህ እምነት ተከታዮች የጥቅሱን ሥርዓት ነጥብ/ነጠላ ሰረዝ / ከቦታው በማንሳትና ከሚከተለው ቃል በኃላ በማድረግ ይዘቱን ሙሉ በሙሉ ለውጠዋል:: ይኸውም «እውነት እውነት እልኃለሁ ዛሬ» የሚለውን «እውነት እውነት እልኃለሁ ዛሬ» በሚል በመተካት ነው:: እንግዲህ እንደነሱ ትምህርት ጌታ በገነት የሚሆነው ከመጨረሻው ትንሣኤ በኃላ መሆኑ ነው::

የክርስቶስን ሰው መሆን ከሚያመለክቱ ጥቅሶች አንዱ በ1ጢሞቴዎስ 3-16 ላይ የተጻፈው ቃለ ነው:: «እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ የይሖዋ ምስክሮች ሲተረጉሙ «የመለኮት ምሥጢር ታላቅ ነው:: እርሱም በሥጋ ተገልጧልና» በማለት እግዚአብሔር የሚለውን ቃለ በመሠረዝ ትርጉሙን አዛብተዋል::

## _የይሖዋ ምክስሮች የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛ ትርጉም_

የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስን ሁሉን ቻይ የሆነ አምላክ ሳይሆን መለኮታዊ ባሕርይ ያለው ንዑስ አምላክ በኒዩ-ፕላቶኒዝም ወይም ግኖስቲሲዝም( Neo-Platonism or Gnosticism) ትምህርት ተፅእኖ ሥር በመውደቃቸው ሊሆን ይችላል:: በዚህ እምነታቸው ምክንያት በዩሐንስ ወንጌል 1-1 ላይ « ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» የሚለውን «ቃልም መለኮት ነበረ» ብለው ተርጉመውታል:: በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉማቸወ በዩሐ. 1-1 ላይ የሚገኘውን አፋልሰው እንደተረጎሙት ሁሉ ብዙ ቃላትንና ሐረጋትን እንደሚስማማቸው አድርገው ቀይረዋል:: ስምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 20-28 «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ......» የሚለውንና አምላክ ሥጋ መልበሱን /በሥጋ መገለጡን/ ቤተ ክርስቲያንን በገዛ ደሙ መዋጀቱንና በትርጉማቸው የመጨረሻውን ሐረግ ጽንሰ ሃሳብ በመለወጥ «በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን» የሚለ ሃሳብ ብቻ እንዲይዝ አድርገዋል::

ከልደትና ከጥምቀት አስቀድሞ በዘመነ ብስራት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም መጥቶ «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» በማለት አብሯታል ይህ በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥም ወልድ «ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር የነበረ የአብ አንድያልጅ» ተብሏል:: በመዝሙረ ዳዊት 2-7 ላይ አብ ስለርሱ ሲመሰክር «አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ » ብሏል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ደግሞም በኩሩን ወደ ዓለም ሲያስገባ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገድ» በማለት ይህንን ደግሞታል::/ዕብ 1-5:6/

የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ክርስቶስ መለኮትዉ ኃይልን የተጎናጸፈው ወይም የተቀዳጀው በተጠመቀ ጊዜ ነው:: ይህ አባባላቸው «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም በህለም ነበረ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም» /ዩሐ. 1-3:10/ ከሚለው ከዩሐንስ ወንጌል ጋር በፍጹም የሚቃረን ነው:: እንግዲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ካልሆነ እንደምን ዓለምን ሊፈጥር ይቻለዋል?

የይሖዋ ምስክሮች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዘላለማዊ የሆነች የማትሞት ነፍስ የለውም:: ነገር ግን በምድር ሣለ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ለአብ ታዛዥነቱን በማሳየቱና በፈተናዎች ሁሉ ሳይረታ በማሸነፋ ዘላለማዊት ነፍስን እንደ ሽልማት ተቀበለ ይላሉ:: እንደነሱ አባባለ ክርስቶስ በመጀመሪያው የሕልውና ጊዜ መዋቲ ሕልውና በታዛዝነት ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው:: እናም አዋላክ /ይሖዋ/ ጊዜው ሲደርስ ለልጁ ታዛዥነት የዘላለማዊ ሕይወት ሽልማት ሰጠው ይላሉ::

ይህ አስተሳሰባቸው በፍጹም ሊሆን የማይችል ነገር ነው:: ምክንያቱም« ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች የተመሰከረለትና ሁሉንም የፈጠረ ወልደ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ዘላለማዊ ሕልውና ይህን ሁሉ ሊያደርግ ይችላል? /መዝ. 109-3

## _ክርስቶስን በተመለከተ የይሖዋ ምስክሮች ኑፋቄ_

- ምንም እንኳን የይሖዋ ምስክሮች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ነው እንዲያውም በኢሳይያስ 9-6 እንደተገለፀወ ኃያል አምላክ ነው የሚል እምነት ቢኖራቸውም ቅሉ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ የሆነው ኃያሉ እግዚአብሔር ነው ብለው አያምኑም :: ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው የይሖዋ ምስክሮች በብዙ አማልክተ የማመን ዝንባሌ እንዳላቸው ነው::

- የይሖዋ ምስክሮች ሰብአ ሰገል በቤተልሔም በጌታችን ፊት ያደረጉት ስግደት የማይገባና የመራቸውም ኮከብ ከሰይጣን የተላከ እደሆነ ያምናሉ::
- የይሖዋ ምክስሮች ክርስቶስ አስቀድሞ በሰማይ ከተፈጠረ በኃላ በዚያው ኖሯል ወደ ምድር እንዲመጣ ያስፈለገበት ዋነኛ ዓላማም ስለ ይሖዋ መንግሥት ለመመስከር ነው ይላሉ:: ይህ አባባላቸው በ325 በኒቂያ በተደረገወ ጉባዔ ላይ በፅኑ ተወግዞ ከነበረወ ከአርዩስ ስህተት ላይ የሚጥላቸወ ሲሆን በወቅቱ በመንፈሳዊ ተጋድሎ አርዩስን በመርታት የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የመሰከረወ የሃይማኖት አርበኛ ቅዱስ አትናቴዎስ ነው::

የይሖዋ ምስክሮች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዳግም ልደቱ መጀመሪያ በሚሆነው ጥምቀቱ ለእግዚአብሔር ልጅነት የተሾመ ነወ በዚህመ የአብ መንፈሳዊ ልጅ በመሆን የይሖዋ መንግሥት ገገር /ንጉሥ/ ሆኗል ብለው ያምናሉ :: የጽሐፍ ቅዱስ ግን በጥምቀት ጊዜ አብ ስለክርስቶስ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደወ ልጄ ይህ ነው » /ማቴ. 3-17/ ብሎ የመሰከረለትና መጥምቁ ዩሐንስም «እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ» /ዩሐ. 1-34/ በማለት ምስክርነቱን የሰጠበት መሆኑን ያረጋግጣል::

- በተጨማሪም ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ ከቶውንም በሥጋ አልተነሣም እንዲሁም በፍጹም በሥጋ በክብር ወደ ሰማይ አላረገም:: ነገር ግን የተሰቀለው ሰውነቱ /አካሉ/ በአምላክ ረቂት ኃይል አማካኝነት በመላእክት ከመቃብሩ ተወስዶ የተደበቀ ሲሆን የተነሣው በመንፈስ ብቻ ነው ይላሉ:: ነገር ግን ይህ ኑፋቄ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤወ በኃላ ለደቀ መዛሙርቱ «እነ ራሴ እንደሆንኩ እጆቼንና እግሮቼን እዩ » /ሉቃ. 24-39 / ካላቸው ጋር በፍጹም የሚቃረን ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ጌታችን « ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ ከማር ወለላም ሰጡት ተቀብሎም በፊታቸው በላ» /ሉቃ. 24-43/ በተጨማሪም የተወጋበትን የቁስሉን ዶታ ቶማስ በመዳሰስ አረጋግጧል::/ዩሐ. 20-27:29
- የትንሣኤ ትክክለኛ ትርጉም የሥጋ ትንሣኤ ማለት ነው:: ምክንያቱም ነፍስ መዋቲ ስላልሆነች ሥጋ ከመንፈስ ጋር በተገናኘ ጊዜ ወይም በድጋሚ በተዋሕደ ጊዜ ትንሣኤ ይሆናል:: ስለዚህ ሥጋዊ አንል የማይነሣ ከሆነ ትንሣኤ የለም ማለት ነው::
- የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስ የተወጋውን አካሉን ይዞ ወደ ሰማይ አላረገም የሚሉበት ምክንያታቸው በአካል ቢያርግ ኖሮ ከመላእክቱ ሁሉ ያንስ ነበር የሚል ደካማ አስተሳበብ ስላላቸወ ነው:: ነገር ግን እኛ የክርስቶስን መወጋት የክርስቶስን ቁስል የምናየው እንደ አካል ጉድለት ሳይሆን እኛን ለመዋጀት የከፈለው የፍቅሩ ምልክት አድርገን ነው:: እናም እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ « .....በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን » እንላለን:: /ኢሳ. 53-5/

የራእይ መጽሐፍም ክርስቶስ« እንደታረደ ምፋ» /ራእ. 5-6/ ቆሞ መታየቱን ይገልጽና « መጽሐፍን ትወስድ ዘንድ ይገባሃል ታርዛልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥት ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው .....» /ራእ. 5-9/ በማለት ካህናቱ ተንበርክከወ ወድቀው እንደሰገዱለት ይናገራል::

## ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ነውን?

የይሖዋ ምክስሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መላእክት ሚካኤል ነው ብለውም ያምናሉ:: እምነታቸውም « ዘላለማዊ ሕይወት ማለት ይህቺ ናት» በሚለ ርዕስ በራእይ ዩሐንስ 12-13-19 በሰጡት ትርጉም ያሰፈሩሲሆን የአምላክ በገና በሚለው መጽሐፋቸው ደግም በዳንኤል 12-1 እንዲሁም ድኅነት በሚለው መጽሐፋቸው በራእይ ምዕራፍ 12-7-9 ውስጥ ባሉት ሃሳቦች ላይ አስተያየታቸውን በሰነዘሩባቸው መጻሕፍቶቻቸው ተንፀባርቋል::

## ለዚህ የምንሰጠው ምላሽ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ 1-3-14 የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ከመላእክት ሁሉ እጅግ በጣም የበለጠ መሆኑን ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል::

1. የክርስቶስ መቀመጫ በላይ በሰማይ በእግዚአብሔር ቀኝ ነው:: /ዕብ. 1-3/ ይህ እውነታ በተጨማሪ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 16-19 እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ 7-56 ላይ በግልፅ የሰፈረ ነው:: አብ ወልድን « ጠላቶችሀን የእግሮችህ መረጋገጫ እስካደርግልህ በቀኜ ተቀመጥ» ብሎታል:: /ዕብ. 1-3 መዝ. 109-1/
2. በዕብራውያን 1-6 ላይ መላእክቱ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚሰግዱ ተገልጿል:: ይኸው ሃሳብ በተጨማሪ በፊልጵ. 2-10 ላይ ተጠቅሷል::
3. ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር« አምላክ ሆይ ኩፋንህ ለዘላለም ነው የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው::» /መዝ. 44-6/ እንዲሁም ስለ መላእክቱ ሲናገር «መላእክቱን መንፈስ የሚየደርግ አገልጋዩቹንም የእሳት ነበልባል» /መዝ. 103-4/ በማለት ተናግሯል::
4. ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝሙር 101-25-25 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ «ፈጣሪ እደሆነ ይናገራል:: ይህም በዩሐንስ 1-3 ላይ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እሱ አልሆነም::» እንዲሁም « በዓለም

ነበረ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም።» ይላል። /ዩሐ. 1-10/ እንግዲህ ጌታችን መላእክቱን ሁሉ ጨምሮ በዓለም ያሉትን ሁሉ እስከፈጠሩ ድረስ ከነዚህ ፍጥረት መሐል የሆነውን ሊቀ መላእክት ሚንኤልንም ያካትታል ማለት ነው።

5. ቅዱስ መጽሐደፍ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የሚከተለውን ያስነብበናል። «ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት» /መዝ. 7-6 ዕብ.2-8/ በተጨማሪም «የሚመጣውን ዓለም ለመላእክት ያስገዛው አይደለምና» /ዕብ. 1-5/ ተብሏል። ጌታችን ስለራሱ ሲናገር «ሥልጣን ሁሉ በሰማጥ በምድርም ተሰጠኝ» ።/ማቴ. 28-18/ እንግዲህ ይህ ሥልጣን በመላእክትም ላይ ጭምር የበላይነት እንዳለው ያረጋግጣል።

## የሚከተሉትን ነጥቦች በተጨማሪነት እናክላለን

1. ሊቀ መላእክት ሚካኤል ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ «ጌታ ይገስጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም ።» /ይሁዳ 9/ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብዙ ሰዎች ውስጥ ርኩሳን መናፍስትን እንዳወጣላቸውና ለደቀ መዛሙርቱም ሀብተ ፈውስን እንደሰጣቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። /ማነ. 10-1:8 ሉቃ 10-17/
2. ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የባሪያን መልክ ይዞ ራሱን ባዶ አደረገ» /ፊል. 2-7/ ሲል መልአኩ ግን በተፈጥሮው የእግዚአብሔር ባርያ መሆኑ ተገልጿል። /ራእ. 19-10/
3. በመጽሐፉ ኢዮብ 1-6 እና 38-7 ላይ መላእክቱ የእግዚእብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩ ሲሆን ጌታችን ግን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ተብሎ በዩሐንስ 3-16 እና 18 በዩሐንስ 1-8 እንዲሁም በ1ዩሐንስ 4-9 ላይ ተገልጿል። ይህም ክርስቶስ አንዱና ብቸኛው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን ያሳያል።
4. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቂቀ መላእክትም ሆኑ ሊቃነ መላእክት ሊናገሩ የማይችሉትን እርሱና አብ አንድ እንደሆኑ ተናግሯል። /ዩሐ. 10-30/
5. ሊቀ መላእክት ሚካኤልም ሆነ ሌሎች ሊቃነ መላእክት ለእግዚአብሔር ብቻ የተለየ ባሕርይ በሆነው ሁሉን ቻይነት ዘላለማዊነት የመፍጠርና ሃሳብን የማወቅ ልዩ ችሎታ እንዳላቸው ሆነው በፍጹም በመጽሐፍ ቅዱስ አልተገለጸም የላቸውምም ።
6. የቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው «መላእክቱ » የእርሱ መሆናቸው ተገልጧል። /ማቴ. 13-41:16-27:24-31/ ይህም ማለት ሊቀ መላእክት ሚንኤልን ጨምሮ መላእክተ በሙሉ ለእርሱ ሚካኤልን ጨምሮ መላእክት በሙሉ ለእርሱ እንደሚታዘዙ የሚያመለክት ነው።

- ሌላው ልናነሣ የምንወደው ነጥብ ደግሞ የይሖዋ ምስክሮች ጌታን እንደ መልአክ መገለጥ እና ጌታን ራሱን እንደ መልአክ ማየትን እንደ አንድ የሚያዩዋቸው ሁለት የተለያዩ ነጥቦች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የጌታ መልአክ መገለይ ማለት እርሱ መልአክ ነው ማለት አይደለም። እንዲሁም በኦሪት ዘፍጥረት 32-24-30 ላይ ጌታ በሰው መልክ ተገልጧል። እና እንግዲህ ይህ ማለት እሱ ሰው ነው ማለት ይሆናል?

## ዘላለማዊቷ ምድራዊ ገነት

የይሖዋ ምስክሮችና የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት እምነት ተከታዮች የጽድቅ ሽልማት ገነት የምትሆነው ምድር ናት ብለው ያምናሉ። ይህንንም በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፡-

- ለተዋጁት ሁሉ በሰማይ ዘላለማዊ መሆኖሪያ ይሰጣቸዋል የሚለ ቃለ ኪዳን የያዘ ጽሑፍ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ የለም።
- እግዚአብሐር ምድርን የሰው ልጆች መኖሪያ ትሆን ዘንድ ሠራት ። ነገር ግን ሰይጣን ምድርን በኃይል ነጥቆ ወሰደ። እናም ምድር ለአምላክ ልጆች እስክትመለስ ድረስ ኃጢአት የመለኮትን ዕቅድ አዘገየ።
- የምድርን ወራሽነት በተመለከተ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃለ ኪዳን ከመንጸቱ በኃላ እውን የሚሆን ሲሆን ኢየሩሳሌምም የመንግሥቲቱ ዋና ከተማ ትሆናለች።
- ሰዎች ሁሉ ገነት በምትሆነው ምድር በደስታ ይኖራሉ። በዚህም «ቤቶችንም ይሠራሉ ይቀመጡባቸውማል ወይኑንም ይተክላሉ ፍሬውንም ይበላሉ።» የሚለው የኢሳይያስ ትንቢት ይፈጸማል።/ ኢሳ. 65-21/

## ለዚህ ኑፋቄ የሚሰጠው መልስ

1. ምድርን ዛፎችንና ቤቶችን እንደሚመግሱ የተገባላቸው ቃለ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገርለት ዘላለማዊ ደስታ ፈጽሞ ተቃራኒ ነው ።«ዐይን የላየችውን ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው» ነው /1ቆሮ. 2-9/
2. የሥጋ ደስተዎች በሙሉ ማለትም መብላት መጠጣት በሰው በተሠሩ ቤቶች ውስጥ መኖርና በመናፈሻ ሥፍራ የሚገኙ ደስታዎች በሙሉ ቁስ አካላዊ /ምድራዊ/ ነገሮች ሲሆኑ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን የሙታን ትንሣኤ በሰማያዊ አካል መሆኑን ነው። /ቆሮ. 15-44:49-50/ ስለዚህ እነዚ ሰማየዊ አካላት እንደምን ምድራዊ የሆኑ ነገሮችን ይወርሳሉ?

3. ለሰወ ልጆች በምድር ላይ የመኖሪያ ሕንፃዎችን ለዘላለም መገንባትና ወይኖችን በማሳዎቻቸወ መትከል የሚቻል አዳደለም:: የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በሙሉ ለዘላለማዊ የምድር ሕይወት የተተነበዩ አይደሉም:: እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሮቹ የገባላቸው ቃል ኪዳን የሰማያዊ ሕይወት ተምሳሌት ናቸው::
4. መጽሐፍ ቅዱስ ይህች ምድር እንደምታልፍና ለሰው ልጆችም በመኖሪያነት እንደማትፀና ይናገራል:: ጌታችንም «በሰማይና ምድር ያልፋሉ::» ብሏል:: /ማቴ. 5-18/ ይህ በተጨማሪ በራእይ መጽሐፍ ላይም ተጠቅሷል::/ራእ.21-1/
5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ « ሰማያዊ መንግሥት » በማቴዎስ ወንጌል የተናገራቸወ ምሳሌዎች ብዙ ናቸው:: /ማቴ. 13 24-31-47:18-23:20-1:22-2:25-1/ በተጨማሪም ስለ ሰማያዊ መንግሥት ከተነገሩት ዐበይቱም እንደሚከተለው ተገልጸዋል::

- «እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የማሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናህ ይባላል የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል» /ማቴ. 5-19/
- «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም::» /ማቴ. 7-21/
- «በሰማያት ዋጋችሁ ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ::» ሐሴትንም አድርጉ::» /ማቴ. 5-12/
- «ስማችሁ በሰማየት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ::» /ሉቃ. 10-20/
- «ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ» /ማቴ 6-20/
- «ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጁ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን::» /2ቆሮ. 5-1:2/ ይህ ጥቅስ «ቤቆችና ሕንፃዎች ይገነባሉ» ከሚለው ሐረግ /ሃሳብ/ ጋር በፍጹም አይስማማም:: በተጨማሪም ቆላ. 1-5: ዕብ. 11-16 ማር.12-25 2ጢሞ. 4-8 ዕብ. 11-16 ማንበብ ይጠቅማል::

6. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያመኑት ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመገናኘት በደመና እንደሚነጠቁ ሲናገር «ከዚያመ በኃላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁለ ጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን::» /1ተሰ. 4-17/ ብሏል:: ጌታም ስለ ዳግም ምጽአቱ ሲናገር «መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፍሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ:: /ማቴ. 24-31/ በተጨማሪም አምላኝችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኃለሁ::» /ዩሐ. 14-3/ ብሏል::

## <u>የይሖዋ ምስክሮች የሰው ነፍስ የማትሞት መሆኗል አያምኑም</u>

የይሖዋ ምስክሮች የሰወ ልጅ በሥጋ ሲሞት ነፍሱም አብራ ትሞታለች በሰው ልጅና በእንስሳት ሞት መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም:: ዘላለማዊነት የይሖዋ ብቻ የተለየ ባሕሪ ነው ብለው ያምናሉ::

እንደነሱ አባባል ዘላለማዊነትን የሚያገኘው ብቸኛው ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ዘመን ፈተናውን የተወጣው ብቻ ነው:: የሰው ነፍስ በተፈጥሮዋ ዘላለማዊ አይደለችም:: ነገር ግን በመንፈሳዊ ውጊያ ካሸነፈች አምላክ ዘላለማዊነትን ይሰጣታል::

የይሖዋ ምስክሮች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የማትሞት ዘላለማዊት ነፍስ አልነበረውም ይላሉ:: ነገር ግን እስከ ሞት ድረስ በእምነቱ በመጽናቱና በተፈተነ ጊዜ በብርታት በማሸነፉ ዘላለማዊ ሕይወትን እንደ ዋጋ ተቀበለ በማለት ያስተምራሉ:: በዚህ ብቻ ሳያበቁ የሰው ነፍስ አትሞትም የሚለውን ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጣው ሰይጣን ዲያቢሎስ ነው:: ይህንንም ለአዳምና ለሔዋን የነገራቸው «ሞትን አትሞቱም» /ዘፍ. 3-4/ ባላቸው ጊዜ ነው:: ይህንን በማለቱ ሰይጣን ውሸታም ነበር:: የሰው ነፍስ ዘላለማዊ ናት የሚለውም በሰይጣን የመጣ የሐሰት ትምህርት እንደሆነ ያምናሉ::

እናም ሰው ከሞተ በኃላ ምንም አይነት ስሜትና ግንዛቤ እንዲሁም ዕውቀት አይኖረውም:: ይህም እስከ ሙታን ትንሣኤ ቀን ድረስ እንደሚቀጥል ይሰብካሉ:: ለዚህ ነው የይሖዊ ምስክሮች ምድራችንን በሥጋ የተለዩ ቅዱሳንን መንፈሳቸውም አብሮ ስለሞተ ምንም ዓይነት ስሜትና ግንዛቤ ስለማይኖራቸው አያማልዱም ብለው የሚያምኑት::

እንደ እነርሱ አባባል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በባሕሪው ዘላለማዊት ነፍስ ስላልነበረችውና ዘላለማዊነትን ያገኘ ው ከአሸናፊነቱ በኃላ በተሰጠው ጸጋ ስለሆነ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አይደለም ብለው ያስተምራሉ::

የይሖዋ ምክስሮች በሕዝቅኤል መጽሐፍ ላይ የተጠቀሰውንና «ኃጢአትን የምታደርግ ነፍስ እርሷ ትሞታለች» የሚለውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ የነፍስን መዋቲነት ለማረጋገጥ ይሞክራሉ:: በዚህ ጥቅስ ውስጥ «ነፍስ» የሚለው ቃል አገላለጽ ልክ በ1ጴጥሮስ 3-20 ላይ ስምንት ነፍሳት የሚለው ስምንት ሰዎችን ለማመልከት ሲሆን ነፍስ የሚለው

*ቃለ ትርጉም እዚህ ላይ «ሰውን» ለማመልከት ነው:: የሰዶም ንጉሥ አባታችን አብርሃምን «ነፍሶቹን ስጠኝ ከብቶቹን ግን ላንተ ውሰድ አለ» /ዘፍ. 14-21/ በተመሳሳይም በሐዋርያት ሥራ 2-41 ላይ «ቃሉንም በደስታ የተቀበሉ ሶስት ሺህ ያህል ነፍሶች ነበሩ::» እንደዚሁም የሐዋርያት ሥራ 27-37 ያዕቆብ 5-19:20:14 1ጴጥ. 1-9 ምሳሌ 25-25 ዘፀ. 31-14 ዘሌዋ. 19-8 ዘፍጥ. 12-5 እና ዘፍ. 3-7 በተጨማሪ ማመሳከር ይቻላል::*

## ለዚህ ትምህርታችው የሚሰጥ ተጨማሪ ምላሽ

1. እግዚአብሔር መዋቲ አይደለም ካልን ሰው በእግዚአብሔር አምሳለ ስለተፈጠረ የሰውም ነፍስ መዋቲ አይደለችም::

2. ሰው እንስሳን አይመስልም::ምክንያቱም እግዚአብሔር በአዳም ውስጥ የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ስላለበት የሰው ልጅ ሕያወ ነፍሰ ነው::/ዘፍ. 2-7/

3. ቅዱስ መጽሐፍ እግዚአብሔር የአብርናም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ ... የሕያዋን አምላክ ነኝ እንጂ የሙታን አይደለሁም /ማቴ. 22-32/ በማለት ይናገራል:: እንግዲያው አብርሃም ይስሐቅ እንዲሁም የዕቆብ በሥጋ ከዚህ ዓለም ከተለዩ ከዘመናት በኃላ እነዚህን ቅዱሳን አንስቶ የ«ሕያዋን» አምላክ ነኝ ካለ የነዚህ ቅዱሳን ነፍሳቸው ከሥጋቸው ጋር ሞቶ አልቀረም ማለት ነው::

4. በራእይ መጽሐፍ ከመሰዊያው በታች የታረዱት ሰዎች እግዚአብሔርን እንዴት ያናግሩ እንደነበርና እግዚአብሔርም እንዴት ይመልስላቸው እንደነበር ተጠቅሷል:: /ራእ. 6-9:11/ እንግዲያው ነፍሳቸው አልሞተም ማለት ነው::

5. የመጀመሪያው ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሲሞት «ጌታ ሆይ ነፍሴን ተቀበል» /የሐዋ. 7-59/ ብሏል:: ይህ ቃል ጌታ እግዚአብሔር ምንም የማያስተውል የማይሰማና የማይናገር በድን ነፍስ ይቀበላለ ማለት እንዳልሆነ ያረጋግጣል::

6. በመጽሐፍ መክብብ ውስጥ ስለሞት «አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ::» /መክ. 12-7/ ተብሎ ተጽፏል:: ወደ ፈጣሪው ተመለሰ ማለትም ሕያው መሆኑን ያመለክታል::

7. በመጽሐፍ ኢዮብም «ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኃላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ እኔ ራሴ አየዋለሁ ዓይኖቼም ይመለከቱታል» /ኢዮ. 19-26:27/ የሚል ቃለ ይገኛል:: ታዲያ ነፍሱ ሙት ወይም በድን ከሆነ እንደምን አድርጎ እግዚአብሔርን ሊያይና ሊያስተውል ይችላል?

8. ቁጥራቸው ብዙ ስለሆኑትና ከሙታን ስለተነሱት ሰዎች ተአምር እንግዲህ ምን እንላለን? /ማቴ. 27-52:54/ በተጨማሪም በሉቃስ 16 ላይ የተገለፀው የባለጠጋው ሰው እና የአልዓዛርን ታሪክ መመልከት ይቻላል::

9. ጌታ በቀኙ የተሰቀለውን ወንበዴ «እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ያለውንና በሉቃስ ወንጌል 23-43 የተጻፈውን ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው የይሖዋ ምስክሮች በለወጡት ትርጉማቸው ላይ «እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ያሉት የተሳሳተ ትርጓሜ ምክንያታዊ እንዳልሆነ ቁልጭ ብሎ ይታያል::

10. «የሰው ሞት» የሚለው ገለጻ ትርጓሜ የሚያመለክተው የነፍስን መሞት ሳይሆን የነፍስን ከሥጋ መለየት ነው::

    የይሖዋ ምስክሮች በሥጋና በነፍ መካከል ያለው ልዩነት ተቀላቅሎባቸዋል:: /2ተሰ. 5-23/ በትንቢተ ሕዝቅኤል ላይ «ኃጢአትን የምታደርግ ነፍስ እርሷ ትሞታለች» /ሕዝ. 18-4/ ማለት ኃጢአትን የሚሠራ ሰው «በእሳትና በዲን ባሕር »/ራእ. 20-10/ ውስይ ዘላለማዊ ሞትን ይሞታለ ማለት ነው::

11. በታቦር ተራራ ላይ ስለሆነው የክርስቶስ መለኮታዊ ክብር መገለጥ እና ስለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ነፍስ ምን እንላለን? /ማር. 9-2:8/ ጌታ ከ1400 ዓመታት አስቀድሞ የሞተውን ነቢዩ ሙሴን በተራራው ላይ አናግሮት ነበር:: /ማር. 9-4/ እና የሙሴ ነፍ ምንም የማይሰማና የማይገነዘብ ሙት ወይም በድን ነበርን?

## የፍጹም ጥፋት አስተምህሮ

የይሖዋ ምስክሮች ኃጢአተኞች ከጻድቃን ተለይተው እንደሚጠፉ እንጂ የሚሰቃዩ መሆናቸውን አይቀበሉም:: ሌላው ቀርቶ ሰይጣን ይጠፋል እንጂ አይሰቃይም:: አባታችን አዳምም አንዴ ስለሞተ ትንሣኤ አያገኝም ይላሉ::

1. በነፍስ ሕያውነት አያምኑም

የይሖዋ ምስክሮች የነፍስ ሕያውነት /የማትሞት ነች/ የሚለው አስተሳሰብ መጀመሪያ የተፈጠረው ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን «ሞትን አትሞቱም» / ዘፍ. 3-4/ ባላቸው ጊዜ ነው ይላሉ:: የሰው ነፍስ እንደ እንስሳ ነፍስ ትጠፋለች:: ሕያውነቷመ ይቆማለ የሚሉ ሲሆን በእነርሱ አመለንከት ዘላለማዊነት የነፍስ የተፈጥሮ ባሕሪ ሳይሆን እግዚአብሔር ለጻድቃን የሚሰጠወ ገጸ በረከት ነው::

2. የይሖዋ ምክስሮች የፍጹም ጥፋት ቅጣት ኃጢአት ለሚያደርጉና ለሰይጣን ጭምር ነው ብለው ያምናሉ:: በትምህርታቸው ሰይጣን ጭምር ነው ብለው ያምናሉ:: በትምህርታቸው ሰይጣን እስከመጨረሻው ይጠፋል ሕያውነቱንመ ይቀማል እንጂ አይሰቃይም ይላሉ:: ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ፍጹም ተቃራኒ ነው:: በራእይ መጽሐፍ ላይ «ያሳታቸውም ዲያቢሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ ለዘላለም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ::» /ራእ. 20-10/ ተብሎ ተጽፏል :: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግራው ለቆሙት እንዳለው ኃጢአተኞች ሁሉ ከዚህ እድል ፈንታ ተካፋዩች ናቸው:: /ማቴ. 25-4/

3. መጽሐፍ ቅዱስ «ዘላለማዊ ስቃይ» አለ እጂ ዘላለማም ጥፋት አላለም::

ሰይጣን እና ጭፍራዎቹ ከሐሰተኞች ነቢያትና ኃጢአተኞች ጋር ሁሉ በአንድነት በእሳትና በዲን የሚቀጡ ሲሆን ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጥአንንና የጻድቃንን ዕድል ፈንታ በግልጽ ተናግሮታል:: «እነዚያ ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ::» /ማቴ. 25-46/ በተጨማሪም ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩመ ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበለ ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀለ ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል:: በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል:: የስቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድርስ ይወጣል ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሉት እረፍት የላቸውም::» /ራእ. 14-9-11/

«እረፍት የላቸውም» የሚለው ሐረግ ልክ በሮሜ 2-8-9 ላይ እንደምናገኘው «መከራና ጭንቀት» የሚለው ሐረግ ከ«ፍጹም ጥፋት» ጋር አይስማማም ወይም አይጣጣምም:: በተጨማሪም ስለጌታ ዳግም ምፅአት በማቴ. 13-41-42 ላይ «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የማያደርጉትን ይለቅማለ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል » ተብሏል:: በርግጥም ፍጹም ጥፋት ከለቅሶና ጥርስ ማፈጨት ጋር አይስማሙም:: እንዲሁም በሉቃስ 16-24 ላይ ስለተጠቀሰውና በነበልባል እሳት በመሰቃየቱ ጣቱን ውኃ ነክሮ በምላሱ ላይ ጠብ እንዲያደርግለትና ቃጠሎውን እንዲያበርድለት አልዓዛርን እንዲልክለት አብርሃምን ከጠየቀው ከባለጠጋው ሰው ታሪክ ጋርም አይስማማም::

4. የጥፋት ጥያቄና የስቃይ አለመኖር ሰዎችን ወደ ግድየለሽነት ይመራቸዋል:: ለዓለማዊ ፍላጎታቸው ሲሉ«... ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ» /1ቆሮ. 15-32/ እንደሚሉት ፈላስፎች የቅጣት አለመኖር ሰዎችን እንዲህ እንዲሉ ያደርጋል::

5. የፍጹመ ጥፋት ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ ራሳቸውን የሚገሉ ሰዎችን ያደፋፍራል::

ራሱን የሚያጠፋ ሰው ምናልባት ከዓለመ መከራና ስቃይ እፎይታ ያገኘ መስሎ ሊሰማወ ይችላል:: ነገር ግን ከሞት በኃላ ነፍስ ገዳይ በመሆኑ ምክንያት የሚጠብቀው ስቃይ መሆኑን ልንጠቅስ እንወዳለን:: ይህን በመፈጸሙ ዘላለማዊ ቅጣት ይጠብቀዋል:: ሆኖም ይህ ሰው የሚጠብቀው ጥፋት ብቻ ቢሆን ኖር ከምድራዊው እንዲሁም ከሞተ በኃላ ከሚጠብቀው ስቃይ ነጻ ይሆን ነበር::

6. ጥፋት ከትንሣኤና ከኃጥአነ ፍርድ በፍጹም ተቃራኒነት አለው::

እግዚአብሔር በብዙ ሺህ ሚሉዩን የሚቆጠሩትን ኃጥአን አስነስቶ «ከኔ ሂዱና ዳግመኛ ሙቱ ልላችሁ አስነሳኃችሁ» የሚለው ምን ለማለት ነው?

ምንም እንኳን የይሖዋ ምስክሮች ሙታን አይነሱም ቢሉም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደርጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፋም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ::» /ዩሐ. 5-28-29/ ያለው ቃልስ? እንደዚሁ በማቴዎስ 25-31 ላይ የተጠቀሰውና ጌታ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው የሚለይበት የፍርድ ትርጉምስ ምንድነው?

7. የፍጹም ጥፋት ቅጣት ለሁሉም ኃጥአን እኩል የሆነ ዋጋ ያሰጣል::

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 16-27 ላይ እንደተገለፀው ጌታ ለእያንዳንድ እንደ ሥራው ዋጋውን እንደሚከፍለው ቢገልጽም የኃጥአን ሥራ በደረጃውና በአስከፊነቱ ይለያያል:: በዚህም ምክንያት ጌታን ስላልተቀበሉት የቅፍርናሆም ሰዎች« ነገር ግን እላችኃለሁ በፍርድ ቀን ካንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል::» /ማቴ. 11-24/ በማለት ተናግሯል::

## በብዙ ትንሣኤ ማመን

ቅዱስ መጽሐፍ ለጻድቃንና ለኃጥአን ለሁሉም አንድ ዓይነት የሆነ ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ሲያስተምር የይሖዋ ምስክሮች ግን በብዙ ትንሣኤ ማለትም ለተለየዩ ዓይነት ሰዎች የሚደረግ ትንሣኤ ሙታን እንዳለ ያምናሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው በመቃብር ያሉት ሁሉ ጽምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣአ ይወጣሉና በዚህ አትደነቁ::» /ዩሐ. 5-28-29/ የይሖዋ ምስክሮች ግን በሚከተሉት የትንሣኤ ዓይነቶች ያምናሉ::

1. የታናሽ መንጋ ትንሣኤ

ይህ ርዕስ የተወሰደው ከሉቃስ ወንጌል 12-13 ሲሆን የሚናገረውም በጠበበው መንገድ ስለሚገቡትና የተመረጡት ጥቂቶች ስለመሆናቸው ነው /ማቴ. 7-14/

የይሖዋ ምስክሮች ይህ ትንሣኤ ለሞቱትና በሕይወትም ለሚገኙት የ144.000ውን ቁጥር ለሚያሟሉት የእነርሱ አባሎች እንደሆነ አድርገው ያስባሉ:: እናም እነዚህ መንፈሳዊ አካል በመያዝ ሰማያዊ ትንሣኤ ያገኛሉ :: ይህ ገለጻ በ1ቆሮ. 15-44 እና 49 ላይ የተጠቀሰ ነው:: ነገር ግን ይህንን የይሖዋ ምክስሮች ከራእ. 7-4 ቢወስዱትም ቁጥራቸው144.000 ስሆነ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንድ ሰው ነው:: በዚህ በተጠቀሰው ውስጥ ያለው ዝርዝር ለይሖዋ ምስክሮችመ ሆነ በራእይ 14-1-5 ለተጠቀሰላቸው አይሠራም::

የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ይህ ትንሣኤ እ.ኤ.አ በ1914 የጀመረ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው:: ነገር ግን ቁጥሩ ገና ስላልተሟላ አሁንም በሕይወት በሚገኙት የይሖዋ ምስክሮች የሚሟላ ይሆናል::

ቁጥራቸው በብዙ መቶ ሚሊዩኖች ከሚቆጠርና ይህ አሃዝም በየትውለዱ ከመደጋገም ብዛት ውስጥ 1/7ኛ ለሚሆኑ ብቻ ሰማያዊ ትንሣአ ይሆናለ ብሎ ማለት የሚቻል አይደለም:: በራእይ 7 የተጻፈውን ካሟላን የሚቀጥለውን ጥቅስ እናገኛለን:: «ከዚህ በኃላ አየሁ እነሆም አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል በሕዝብና በነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ ነጭ ልብስመ ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ በታላቅም ድምፅ እየጮኹ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው አምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ:: መላእቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር በዙፋኑም ፊት በግንባራቸወ ተደፋ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ አሜን በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን አሜን አሉ::

ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ እንዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ:: እኔም ጌታ ሆይ አንተ ታውቃለህ አልሁት:: አለኝም እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውንም አጥበወ በበጉ ደም አነጹ::» /ራእ. 7-9-15/

2. ምድራዊ ትንሣኤ

ይህንን ትንሣኤ «የሌላው በግ» ትንሣኤ በማለት የማጠሩት ሲሆን በዚህ ትንማኤ የሚንተቱ ምድራዊ አካልን ይዘው በምድር ላይ የሚቀሩና 144.000 ሺዎቹ ከሰማይ የሆነው የሚያስተዳድሯቸው ሰዎች ናቸው::

ከነዚህ የምድር ትንሣኤ ከማያገኙት መካከል በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱትን ጻድቃን ማለት አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብና ዳዊትን የሚያካትት ሲሆን «የምድር ለዑካን» በመባል ይታወቃሉ::

ይህ ትንማኤ በተጨማሪ ክፉ አድራጊዎችን የሚያካትት ሲሆን አንድ ሺህ ዓመት ለመፀፀቻ ጊዜ ዕድለ ይሰጣቸዋል::

ለነዚህ ምድራዊውን ትንሣኤ ለሚያገኙት የጽድቅ አገዛዝ የሚቃቃምላቸው ከመሆኑም በላይ በሰማያዊ መንግሥት ሕግ «ጥላ» ሥር ሆነው ያስገባሉ ልጆችንም ይወልዳሉ::

3. የይሖዋ ምስክሮች አባል ላልሆኑትና ጻድቅ ለሆኑት የሚደረግ ትንሣኤ

እነዚህ በዚህኛው ወገን የተካተቱት በሁለተኛወ ሺህ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለተኛውን ትንሣኤ የሚያገኙ ናቸው::

የይሖዋ ምስክሮች የፍርድ ቀን አንዱ ሺህ ዓመት እንደሆነ ሲናገሩ በተጨማሪም ፈጽሞ ትንሣኤ የማያገኙ እንዳሉም ያስተምራሉ:: ከእነዚህም አንዱ የሞተውና እንዳይነሣ የተቀጣው አዳም ይገኝበታል::

## መንፈስ ቅዱስ አካል ወይስ ኃይል?

የይሖዋ ምክስሮች መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አንዱ አካል መሆኑን ይክዳሉ:: በፈንታው መንፈስ ቅዱስ የይሖዋ ኃይል ነው በማለት ያምናሉ::

ላዚህ አመለንከታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለመንፈስ ቅዱስ የተጻፈወ ቃል መንፈስ ቅዲስ የሥላሴ አንዱ አንለ መሆኑን ያረጋግጣል::

- <u>*መንፈስ ቅዱስ ይናገራል*</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱሳን ደቀመዛሙርት እንደተናገረው «አሳልፈውም ሲስጡአችሁ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኃልና እንዴት ወይስ ምን እድትናገሩ አትጨነቁ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም::» /ማቴ. 10-20/ ሐዋርያወ ቅዱስ ጳውሎስም« ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመረበትም አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት ምድረ በደ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ::» ብሏል:: /ዕብ. 3-7-9/ እንዲሁም «እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኃቸው ሥራ ለዩልኝ አለ» /የሐዋ. 13-2/ ስለዚህ ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረደው መንፈስ ቅድስ ይናገርል እንዲሁም ይጠራል ማለት ነው::

- <u>*መንፈስ ቅዱስ ያስተምራል ያስታውሳል ይመራል እንዲሁመ ይፈርዳል*</u>

ጌታ ለደቀመዛሙርቱ ስለመንፈስ ቅዱስ የነገራቸው ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው:: «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነወ አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኃል እኔም የነገርኃችሁን ሁሉ ያሳስባችኃል::» /ዩሐ. 14-26/ እንዱሁም «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኃል የሚሰማውንም ይነግራችኃል::» /ዩሐ. 16-13/ በሌላም ሥፍራም «እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት ስለጽድቅም ስለፍርድም ዓለምን ይወቅሳል::» /ዩሐ. 16-8/

- <u>*አማንያንን በኅብረትም ይሁን በነጠላ ይመራቸዋል*</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው::» /ሮሜ 8-14/ በማለት ተናግሯል::

- <u>*መንፈስ ቅዱስ እረኞችን ያሰማራል*</u>

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፊሶን ሊቀ ጳጳሳ ሲናገር «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::» /የሐዋ. 20-28:13-2/

- የአገልጋዩቹን መንገድና እንቅስቃሴ የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ስለሐዋርያው ቅድስ ጳውሎስና አብረው ስለነበሩ ሰዎች ሲናገር «በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለከለከላቸወ በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ በሚስያም አንጻር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢታንያ ይሄዱ ዘንድ ሞከሩ የኢየሱስ መንፈስም አልፈቀደላቸውም::» /የሐዋ. 16-6-7/

- <u>*መንፈስ ቅዱስ አማንያንን ያፅናናል ይረዳል*</u>

ጌታችን መጽፅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኃል» /ዩሐ. 14-16/ ብሏል:: እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይናገር መቃተት ይማልድልናል::» /ሮሜ 8-26/ መንፈስ ቅዱስ ለአማንያን የሚናገር የሚያስተምር የሚያስታውስ የማያናግር የማፈርድ እንዲሁመ የሚያሰማራ እንቅስቃሴአቸውን የሚወስን የሚረዳቸው እንዲሁም ገላጭ ከሆነ የሥላሴ አንዱ አካል መሆኑን ማመን አይህርብንም? እንደ ኃይልነቱ ግን መንፈስ ቅዱስ በአማንያን ላይ መውረዱ የሚያስከትለው ውጤት ነው:: «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» /የሐ. 1-8/ የመንፈስ ለአማንያን ያጎናጽፋል::

**የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ !!!**